10ኛ ዓመት ቁጥር 41
10th Year No. 41

ባህር ዳር ሕዳር 20 ቀን 1997 ዓ/ም
Bahir Dar 29 Nov., 2004

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ህግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

1324
ያንዱ ዋጋ ብር 2.00
Unit price ---------

ማውጫ

የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ

Contents

The Revised Amhara National Regional State Judicial Administration Commission Establishment (amendment) Proclamation

አዋጅ ቁጥር 111/1997 ዓ.ም

የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በሥራ ላይ ያለውንና የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 69/1994 ዓ.ም የክልሉ ሕብረተሰብ ከዳኝነት አካላት ለሚጠብቀው የፍትህ አገልግሎት ውጤታማ፣ ተፈፃሚነትና የየደረጃው ፍ/ቤቶች ዳኞች ለሚጠበቅባቸው የሙያ ሥነ-ምግባር ደረጃ አጠባበቅ በሚያግዝ መልኩ እንደገና ማሻሻል በማስፈለጉ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገመንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

Proclamation No. 111/2004

A Proclamation Issued to provide for the Amendment of the Revised Amhara National Regional State Judicial Administration Commission Establishment Proclamation

WHEREAS, it is necessary to re-amend the Revised Amhara National Regional State Judicial Administration Commission Establishment Proclamation No.69/2002, which is in effect, in a way to the effective execution of the justice service that societies of the Region expect from the judicial organs and to the observance of the professional ethical standard which is required from court judges at each level;

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Region, in accordance with the power vested in it under Article 49 Sub-Article 3/1/ of the Revised Constitution of the National Region, hereby issues this proclamation.

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 111/1997 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. **ማሻሻያ**

የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 69/1994 ዓ.ም እንደሚከተለው በዚህ አዋጅ ተሻሽሏል::

ሀ. ከአዋጁ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2 የገባ ሲሆን በዚሁ አዲስ ድንጋጌ መግባት ምክንያት ንዑስ አንቀጽ 2፣ 3፣ 4 እና 5 የነበሩት እንደቅደም ተከተላቸው 3፣ 4፣ 5 እና 6 ሆነው ተሸጋሽገዋል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ቁጥር "ሠ" ሥር የሰፈረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባኤው በአዋጁ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ቅሬታ ባይቀርብባቸውም የክልሉን ሕዝብ የፍትህ ስሜት እንደሚጐዱ የሚያምንባቸውንና በስር ንዑስ ጉባኤዎች ውሣኔ የተሰጠባቸውን የመጀመሪያ ደረጃ የዲሲፕሊን ጉዳዮች በራሱ አነሣሽነት ከመመርመርና እንደገና ተጣርተው እንዲታዩ ከማድረግ ወይም ራሱ አይቶ ከመወሰን አይታገድም::

ለ. የአዋጁ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ተሻሽሎ ከዚህ በታች በተመለከተው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 1 ተተክቷል::

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as "The Revised Judicial Administration Commission Establishment Proclamation Re-amendment Proclamation No. 111/2004."

2. **Amendment**

The Revised Amhara National Regional State Judicial Administration Commission Establishment Proclamation No.69/2002 is hereby amended by this proclamation as follows:

A. The following new sub-Article 2 is hereby inserted next to sub-Article 1 of Article 6 of the proclamation and sub-Articles 2, 3, 4 and 5 are sequentially arranged being 3, 4, 5 and 6 due to the insertion of the stipulation of this sub-Article.

2. Without prejudice to the stipulation provided in under letter "F" of sub-Article 1 of this Article, the Commission shall not be barred from inquiring, causing re-investigation or making decision by itself on first level disciplinary cases which it believes that they hurt the feeling of the people of the Region towards justice and those to which decision is made by lower sub-Commissions, though not grievances are lodged against such cases pursuant to sub-Article 3 of Article 11 of the proclamation.

B. The stipulation of sub-Article 1 of Article 11 of the proclamation is hereby amended and replaced with new sub-Article 1 indicated herein under.

1. ጥፋት ፈጽመው በተገኙ የዞን ከፍተኛና የወረዳ ፍ/ቤቶች ዳኞች፣ ሬጅስትራሮችና ተከላካይ ጠበቆች ላይ አስፈላጊውን የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ይወስዳል፤ ማናቸውንም እርምጃ በወሰደ በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለክልሉ ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ሰብሳቢ በጽሁፍ ያሳውቃል፤ ሆኖም የተፈጸመው ጥፋት ዳኛውን ከሥራ የሚያስነሣ ሆኖ ሲገኝ ለጊዜው ከሥራ አግዶ ደመወዙን እየከፈለ ጉዳዩን ከተገቢው የውሣኔ ሃሳብ ጋር ለክልሉ ጉባኤ ያስተላልፋል።

1. Take the necessary disciplinary measure against Zone high court judges and *wordea* court judges, registrars and defense lawyers; and notify in writing to the chairperson of the Regional Judicial Administration Commission within fifteen days the decision taken thereto; however, where the offence committed warrants the removal of the judge from his duty, it shall suspend the judge from duty, pay his salary and transfer the case to the Regional Commission together with appropriate recommendation.

3. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
ሕዳር 20 ቀን 1997 ዓ.ም

ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት

3. **Effective Date**

This Proclamation shall come into force commencing the date of its publication in the *Zikre Hig Gazetta* of the Regional State.

Done at Bahir Dar,
This 29 day of Nov. 2004

Yosef Retta
President of the Amhara National Region